

አዲሱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ገጽ 3



የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምና ድጋፍ አገልግሎት

ገጽ 4

የወራት ስያሜ እና ትርጉማቸው

ገጽ 5



# ገቢያችን ህልውናችን

የገቢዎች ሚኒስቴር Ministry of Revenues

14ኛ ዓመት | መስከረም 2016 ዓ.ም | ቁጥር 165 | በነፃ የሚታደል


## የታክስ አስተዳደሩን ለማዘመን የዓለም ባንክ ድጋፍ

**በዳንኤል አበበ**

ገቢዎች ሚኒስቴር በተለያዩ ጊዜያት የገቢ አሰባሰቡን እና አሠራሩን ለማሻሻል የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ለዚህ ደግሞ በመንግሥት እና በተቋሙ አቅም የሚደረገው እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ከፋዮች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት እና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ ያስፈልጋል። በዚህ መሠረትም አሁን ለተደረሰው ዘመናዊ የታክስ ሥርዓት የነዚህ አካላት ሚና ከፍተኛ ነበር፤ ወደፊትም ይኸው ይቀጥላል።


በዚህ ረገድ ሰሞኑን ዓለም ባንክ የኢትዮጵያን የታክስ ስርዓት ለማዘመን እየተሠራ ለሚገኘው ሥራ ድጋፉን ለመስጠት ከገቢዎች ሚኒስትር ጋር ውይይት አካሒዷል። አስተዳደሩን ማዘመን ወጪ ቆጣቢ እና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ስለሚያስችል በተግባራዊ የፕሮጀክት ሀሳብ ላይ ነው ውይይቱ ያተኮረው።

የኢትዮጵያ የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ጋር ያለውን ጥምርታ ለማሳደግ ያግዛል በተባለው ፕሮጀክት የኢትዮጵያን የታክስ ፖሊሲ መሠረት እንደሚያደርግ በውይይቱ ተጠቁሟል። ለዚህም የሪፎርም ሃሳቦችን ማመንጨትን፤ ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ እና ተደራሽ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት በቴክኖሎጂ ማስደገፍን እንዲሁም ለታክስ ከፋዮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን የጥራት ደረጃ ማሻሻልን እንደሚያካትት ታውቋል።

የታክስ አስተዳደሩን... ወደ ገጽ 2 ዞሯል




በዓለም ባንክ የኢትዮጵያ ዳይሬክተር ኦስማን ዲኔ እና የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ፤



ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ ከዓለም ባንክ ልዑካን ጋር፤

## እንዘምን

በአገራችን ታክስን አሳውቆ የመክፈል ባህል እያደገ መጥቷል። ግብር ከፋዮች ይህን ማድረጋቸው አገራቸውን የመውደዳቸው አንዱ መገለጫ ነው። ያለገቢ አገርም የምትፈልጋቸውን መሰረተ-ልማቶች እና ግብዓቶች አሟልታ ለዜጎቿ ለማቅረብ አቅም አልባ ትሆናለች። ኢኮኖሚ ጉልበት ነው። ኢኮኖሚው ካላደገ ዜጎች ይበልጥ ተስፋ ቢሶች እና እርዳታ ጠባቂ ይሆናሉ። ኢኮኖሚውን ማሳደግ የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የባላሃብቶችም ድርሻ እጅጉን ከፍተኛ ነው።





መንግሥት ግብር ከፋይ ዜጎችንና ባለሃብቶችን መንከባከብ ግዴታው ነው። ከነዚህ የመንግሥት ግዴታዎች ውስጥ ለግብር ከፋዮች ግብራቸውን እንዲከፍሉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው። በመሆኑም የገቢዎች ሚኒስቴር ኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴን በመጋቢት 2011 ዓ.ም. በአስር ድርጅቶች ላይ የሙከራ ትግበራ አድርጎ ውጤታማ ሆኗል። ከጥር 2012 ዓ.ም.ጀምሮ ደግሞ በአዲስ አበባ ያሉ ሁሉም የገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደክፍያ ሥርዓቱ (e-payment) በመግባት ተግባራዊ ተደርጓል።

አሁን ይህ የክፍያ ዘዴ በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተግባራዊ ተደርጓል። ተገልጋዮችም ባሉበት ቦታ ሆነው ግብራቸውን መክፈል እንዲችሉ በመደረጉ ብዙ እንግልት እንዲቀርላቸው አድርጓል።

በመሆኑም ግብር ከፋዮች የኤሌክትሮኒክስ የክፍያ ዘዴን በመጠቀም ከጥር 2012 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጳጉሜን 6/2015 ዓ.ም ድረስ ከ156 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል። ከዚህም ውስጥ ከ4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ የተሰበሰበው በቴሌ ብር የክፍያ ዘዴ እንደሆነ የገቢ ሒሳብ ማጠቃሌ ቡድን አስተባባሪዋ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ አሸናፊ ተናግረዋል።

ስለዚህ፤ ግብር ከፋዮች የሚዘምነውን የአሠራር ሥርዓት እየተከተሉ ግብራቸውን በወቅቱ እንዲከፍሉ በማድረግ ለአገራቸው እድገት የራሳቸው ድርሻ መወጣታቸው ተገቢ ነው።

## 13ኛው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት



አቶ መስፍን ሺመልስ
በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የታክስ ስሌት ቡድን መሪ፤



ወ/ሪት መቅደስ ተፈራ፤

የገቢውን ዘርፍ እንዲመራ ሃገራዊ ኃላፊነት የተሰጠው የገቢዎች ሚኒስቴር ተገልጋይ ተኮር አገልግሎት ለመስጠት በተለያዩ የሃገሪቱ ክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ሚኒስቴሩ በክልሎች አምስት፣ በአዲስ አበባ ሰባት እና በድሬደዋ አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አሉት።

ከነዚህ መካከል 13ኛ ሆኖ ሐምሌ 1/2015 ዓ.ም አዲስ አበባ ውስጥ የተቋቋመው የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነው። ጽ/ቤቱ የተቋቋመበት ምክንያት የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ላይ የሚስተናገዱት ግብር ከፋዮች ብዛት መስተንግዶው ላይ ጫና ስላሳደረ ነው። ሌላው ደግሞ ከአነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደ መካከለኛ የሚያድጉትን እንዲያስተናግድ ታስቦ ነው።

ምቹ የሥራ አካባቢን ታሳቢ አድርጎ ተቋቋመው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተቋቋመበት በአጭር ጊዜ ውስጥ አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። በዚህም መሠረት ባለፉት ሐምሌ እና ነሐሴ 2.56 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ አቅዶ 2.41 ቢሊየን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 94 በመቶ ማሳካት መቻሉ ተጠቃሽ እና የበጀት ዓመቱን የገቢ ዕቅድም ለማሳካት እንደሚችል ማሳያ ነው።

13ኛው ቅርንጫፍ ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# ርዕሰ አንቀጽ




## ስተሻለ አገልግሎት አሰጣጥ

የገቢዎች ሚኒስቴር፤ «በ2022 ዓ.ም. ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት» የሆነውን ራዕዩን ከግቡ ለማድረስ በርካታ የለውጥ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑ ይታወቃል። ከነዚህ መካከል አሠራሩን በዘመናዊ መልኩ ለማደራጀት ከታክስ ማሳወቅ እስከ መክፈል ያሉትን በኤሌክትሮኒክስ መንገድ የማከናወን ተግባሩን በስፋት በማካሔድ ላይ ነው። ግብይቶች በደረሰኝ የሚከናወኑበት መንገድ በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እየታገዘ ነው። የታክስ ትምህርት ሥራዎችም በማስተማሪያ ሰነዶች (በሞጁሎች) ተዘጋጅተው በሁሉም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተጠናክረው በመሰጠት ላይ ናቸው። በጉምሩክም በኩል የወጪና ገቢ ዕቃዎች የሚስተናገዱበት ሥርዓት ዘመናዊነትን እንዲላበስ በርካታ ተግባራት ተሠርተዋል፤ እየተሠሩም ነው። እንዲሁም የኮንትሮባንድ ክትትሉ እና ቁጥጥሩ በየጊዜው በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ እየተደረገ ነው።

እነዚህ ሁሉ ማሻሻያዎች ግን ምቹ የሥራ አካባቢዎች ወይም ቦታዎች ካልተደራጁላቸው እና ተገልጋዮችም በተመቸ ሁኔታ ካልተስተናገዱ ፋይዳቸው የተሟላ ስላልሆነ ጎን ለጎን ይኸው እየተሠራ ይገኛል።

ምቹ የሥራ ሁኔታን ለማደራጀት ከገቢዎች ሚኒስቴር እና ከጉምሩክ ዋና መ/ቤቶች የተጀመረው ማሻሻያ ውጤት እየታየበት ነው። ሁለቱም ተቋማት መገኛቸውን አማካይ ቦታ እንዲሆን ከማድረግ ጀምሮ ሕንጻዎቻቸው ለተገልጋዮችም፣ ለሠራተኞችም አገልግሎት ምቹ እንዲሆኑ ውስጣዊ ይዞታቸው ሳቢ እንዲሆ አድርገዋል።

ምንም እንኳን ብዙዎቹ የገቢዎች ሚኒስቴር ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኪራይ ሕንጻዎች ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ቢሆኑም በሒደት ኪራይ እንዲወጡ አዳዲስ ግንባታዎች እየተደረጉላቸው ይገኛል። በዚህ በኩል ከአዲስ አበባ ውጪ የመቀሌ፣ የባህርዳር፣ የአዳማ፣ የሀዋሳ እና የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ግንባታ ከግማሽ እስከ ማጠናቀቅ ደረጃ ደርሰዋል።

ከዚህ ሌላ ቀድሞ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ቦታዎች እና ሕንጻዎች ለአገልግሎት አመቺ ባለመሆናቸው የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር አንድ እና የምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደተሻለ ቦታ ተዛውረዋል። ቀደም ሲል ደግሞ የከፍተኛ ግብር ከፋዮች እና የሰሜን ምዕራብ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ምቹነታቸው እንዲረጋገጥ ተደርጎ በመደራጀታቸው ለደንበኞች ደረጃውን የመጠነ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርጓል።

ደንበኞች አገልግሎት ለማግኘት ሲመጡ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን መኪና ላላቸው የመኪናቸውም መቆሚያ ቦታ በቂ እና አስተማማኝ መሆን ስለሚገባው መ/ቤቱ ይህንን ጭምር ከግንዛቤ ያስገባ አደረጃጀትን የመከተል አቋም አለው። ለዚህ እና በኪራይ ምክንያት መሠረተ-ልማቶች ዝርጋታን እንደ ተቋሙ ፍላጎት ለማድረግ ያላስቻለውን እንዲሁም እየወጣ ያለውን የኪራይ ዋጋ ለማስቀረት ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሁሉም ጽ/ቤቶች የየራሳቸው ሕንጻ ባለቤቶች የሚሆኑበት ዕቅድ ወደተግባር ስለተገባ አሁን ያለው ውስንነት ታሪክ ሆኖ ይቀራል።

ገቢዎች ሚኒስቴርም ሆነ ጉምሩክ ኮሚሽን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃቸውን ለማሳደግ እያሳዩት ያለው የለውጥ እርምጃ ለተሳካ የገቢ አሰባሰብ ብቻውን ውጤት ስለማያመጣ ግብር ከፋዮችም በሁሉም ማሻሻያ መስኮች ከነርሱ የሚጠበቀውን ሁሉ እንዲወጡ አደራችንን እናቀርባለን።


ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ ቁጥር 164

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ ሰብሳቢ
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ
እታገኝ አቦሰጥ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 011-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia
ለታክስ እና ለጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199


## የታክስ አስተዳደሩን ለማዘመን ...

ከገጽ 1 የዞረ

ፕሮጀክቱ ከፌደራል ባሻገር በክልሎች በሚገኙ የታክስ ሰብሳቢ አደረጃጀቶች ላይ በወጥነት መተግበር እንዳለበት የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ በውይይቱ ላይ አሳስበዋል። የፕሮጀክቱ ዓላማዎች ከኢትዮጵያ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ እና በመካከለኛው ዘመን ከተያዘው የልማትና የኢንቨስትመንት ዕቅድ ጋር መጣጣም እንዳለበት አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም በፕሮጀክቱ የዲዛይን ምዕራፍ እስካሁን የታክስ ስርዓቱን ለማዘመን የተሠሩ ሥራዎች እና ሌሎች ጅምሮች ተገምግመው መካተት አለባቸው ብለዋል። በሒደቱ የሥራ መደጋገም እና የሃብት ብክነት እንዳይከሰት በኢትዮጵያ የታክስ አስተዳደር ማዘመን ላይ ሌሎች አካላት እየሠሯቸው ከሚገኙ ሥራዎች ጋር መናበብ እና መቀናጀት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

የፕሮጀክት ዲዛይኑን ለማዳበር የገቢዎች ሚኒስቴር እና የዓለም ባንክ ባለሙያዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ የተለያዩ ዐውደ-ጥናቶችን እንደሚያካሒዱ በውይይቱ ላይ ተገልጿል።

የዓለም ባንክ የሃገር ውስጥ ዳይሬክተር አስማን ዲኔ፤ ድርጅታቸው በኢትዮጵያ በርካታ ተግባራትን ለማከናወን የረጅም ጊዜ ፕሮጀክት ቀርጻ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል ብለዋል። ፕሮጀክቱ ትኩረቱን የሚያደርግባቸው ጉዳዮችም ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ዘመናዊ አስተዳደርን ማስፈን፣ በታክስ እና የሀገር ውስጥ ምርት እድገት የሚስተዋለውን ክፍተት ማጥበ እና የታክስ ምንጮች የሚያድጉበት ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሆኑ ጠቁመዋል። እንዲሁም የታክስ አስተዳደሩን ማዘመን እና ለግብር ከፋዮች የሚሰጡ አገልግሎቶችን በጥራት ማሻሻል እንደሆነ አመልክተዋል።

ፕሮጀክቱ ሥራውን ለመጀመር የዝግጅት ሥራዎችን በመሥራት ላይ ስለሚገኝ ለፕሮጀክቱ ተፈጻሚነት የገቢዎች ሚኒስቴር ድጋፍ እንደማይለየው እምነት አለን ብለዋል።

## የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ...

ከገጽ 4 የዞረ

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**15. Z-report በየቀኑ ሳስማውጣት የሚቀርብ ጥያቄ**

- ከተፈቀደላቸው የሥራ ዘርፎች ውጭ መሆን፤
- ዋና ምዝገባ፣ ንግድ ፈቃድ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተደዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**16. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ FD ስህተት የአድራሻ ለውጥና ማስተካከያ ለማድረግ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የንግድ ፈቃድ ኮፒ፤
- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤
- ሰርቪስ ቡክ፤
- ዜዴ ሪፖርት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**17. ከክልሎች የሚቀርብ የመረጃ የአገልግሎት ጥያቄ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ከክልሎች የተጻፈ ደብዳቤ፤
- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤
- መረጃው የሚፈለግበት ዘመን፤
- የንግድ ፈቃድ ኮፒ፤

**የአገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**18. የታክስ ምጣኔ ለውጥ የአገልግሎት ጥያቄ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የንግድ ፈቃድ ተመዝጋቢ ከሆኑ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**19. የመብራት መጥፋትን፣ የማሽን ብልሽትን ለማስታወቅ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ችግሩን ማስታወቅ/ በስልክም ሆነ በአካሌ፤
- የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም መግለፅ፤
- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## 13ኛው ቅርንጫፍ ...

ከገጽ 1 የዞረ

አቶ መስፍን ሺመልስ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የታክስ ስሌት ቡድን መሪ ናቸው። ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደሥራ ቢገባም የአንዳንድ ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በፍቃደኝነት አሳውቀው ያለመክፈል አዝማሚያቸውን ስለታዘበ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሠርቶ ለውጦችን እንዳገኘ ጠቁመዋል። ከዚህ ውጪ ግን አብዛኞቹ የሕግ ተገዢነትን እየተከተሉ በመሆናቸው በሁሉም መስክ ተስፋ ሰጪ ውጤት እንዲመዘገብ አስችለዋል ብለዋል።

ለስኬቱ ከግብር ከፋዮች ሌላ የሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊዎች፣ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሠራተኞች እና ባለድርሻ አካላት ሚናቸው ከፍተኛ እንደነበር ጠቁመዋል።

ወ/ሪት መቅደስ ተፈራ አገልግሎት ፍለጋ ወደ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የመጣች ተገልጋይ ነች። ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ አዲስ ቢሆንም አገልግሎት አሰጣጥ ላይ እንደ አዲስ ባለመሆኑ መረካቷን ትናገራለች።

በቀጣይም ከዚህ የተሻለ እና ዘመኑ የደረሰበትን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ እንዲከተል የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን እንዲጠቀም አሳስባለች።

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በያዝነው በጀት ዓመት በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ በመጠናከር 22 ቢሊየን 285 ሚሊየን 564 ሺህ 624.97 ብር ለመሰብሰብ አቅዶ እየሠራ ይገኛል።

እንግዶችን

አዘጋጅ:- ሺመልስ ሲሳይ

# አዲሱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

**የገቢዎች ሚኒስቴር በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች 13 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያሉት ሲሆን ስድስቱ የሚገኙት በአዲስ አበባ ነው። እነርሱም የከፍተኛ፤ የመካከለኛ ቁጥር አንድ እና ሁለት፤ የምሥራቅ፣ የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ አነስተኛ ግብር ከፋይ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ናቸው። ከአዲስ አበባ ውጪ ደግሞ በመቀሌ፣ በባህርዳር፣ በኮምቦልቻ፣ በአዳማ፣ በጅማ፣ በሀዋሳ እና በድሬዳዋ ይገኛሉ።**

**ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በማስፋፋት በኩል አዲስ አበባ ላይ የግብር ከፋዮች ገቢ እያደገ ሲሔድ እና ቁጥራቸው ከሚስተናገዱበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አቅም በላይ ሲሆን አዳዲስ ት/ቤቶች ተከፍተው አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ። ከነዚህ መካከል አዲስ ተዋቅሮ አገልግሎቱን ሐምሌ 1/2015 ዓ.ም. የጀመረው የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነው። ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን በከፍተኛ አመራርነት እንዲመሩት አራት ሴቶች የተሾሙ ሲሆን አንዷ ሥራ አስኪያጅ እና ሦስቱ ምክትል ሥራ አስኪያጆች ናቸው።**

**ከተቋቋመ በኋላ በአስቸኳይ ወደ መደበኛ ሥራው የገባው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በነሐሴ 2016 ከታቀደለት በላይ ገቢ በመሰብሰብ ቀጣዮቹን ወራት ላይ ተስፋ እንዲጣልበት አድርጓል። በነዚህ እና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ሠብለ ሐጎስ ቀጣዩን ማብራሪያ ሰጥተውናል።**

**ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን መክፈት ለምን አስፈለገ?**

*የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን መክፈት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ለግብር ከፋዮች ፈጣን፣ ተደራሽ እና ፍትሃዊ አገልግሎት ለመስጠት ታስቦ ነው። በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር አንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የግብር ከፋዮች ብዛት ከ8ሺ በላይ ነበር። ካለው የቢሮ አደረጃጀት እና የጽ/ቤቱ የሰው ኃይል የማስተናገድ አቅም አኳያ ይህን ያህል ግብር ከፋይ በአንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስተናገድ ስለማይቻል ተጨማሪ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መክፈት አስፈልጓል።*

**በስንት ሠራተኞች እና ግብር ከፋዮች ነው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራውን የጀመረው?**

*ሥራ የጀመርነው ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ከሚያስፈልገው የሰው ኃይል በ52 በመቶዎቹ ብቻ ነው። እነዚህ የተሟሉልን ቀደም ሲል ከነበሩት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ከዋናው መ/ቤት ነው። ወደኛ የተመደቡት ሠራተኞች በባህሪያቸውም ሆነ በሥራ አፈጻጸማቸውም የተሻሉ በመሆናቸው በአጭር ጊዜ ቆይታችን መልካም ውጤት አይተንባቸዋል።*

*በግብር ከፋዮች በኩል ካለን የሰው ኃይል እና የቢሮ አደረጃጀት አኳያ የተመደቡልን 4ሺ7 ግብር ከፋዮች ናቸው። የነዚህን ግብር ከፋዮች ፋይል ቀድሞ ከነበሩበት አምጥቶ የማደራጀት ሥራ ተጠናቆ ነው ሥራ ጀመርነው።*

**በ2016 በጀት ዓመት ምን ያህል ገቢ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሲሰበሰብ ታቅዷል? ያለፉት ሁለት ወራት አፈጻጸምስ ምን ያህል ነው?**

*ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በ2016 በጀት ዓመት እንዲሰበስብ የታቀደለት 22 ቢሊየን 285 ሚሊየን 564ሺ 624.97 ብር ነው። ዕቅዱ ለየወራቱ ይመነዘራልና ባለፉት ሁለት ወራት 2 ቢሊየን 562 ሚሊየን 839ሺ 931.87 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ2 ቢሊየን 411 ሚሊየን 661ሺ 426.57 ብር በመሰብሰብ የዕቅዱ 94 በመቶ ተሳክቷል።*



ወ/ሮ ሠብለ ሐጎስ
የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ፤

**ዓመታዊ ዕቅዱን ለማሳካት ምን ምን ዝግጅቶች ተደርገዋል?**

*ዕቅዳችንን ለማሳካት ከሁሉ በፊት ለግብር ከፋዮቻችን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ግብር ከፋዮች ያሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ በመስጠት ላይ እንገኛለን። ይህንን በማድረጋችን ባለፉት ጊዜያት ውጤት አግኝተንበታል።*

*ሌላው እያከናወንነው ያለው ተግባር የሕግ ማስከበር ሥራ ነው። ግብራቸውን በወቅቱ የሚያሳውቁ በርካታ ግብር ከፋዮች የመኖራቸውን ያህል በግዴለሽነት የማያሳውቁ በርካታ ግብር ከፋዮችም አሉ። እነዚህን ወደ ሕጋዊ መንገድ እንዲገቡ በተደረገው ጥረት አብዛኞዎቹ ወደ ሕጋዊነት የገቡ ቢሆንም አሁንም ወደ ህጋዊነት ያልገቡት ለማስገባት በትጋት እየሠራን እንገኛለን።*

*ምንም እንኳን እርምጃ መውሰድ አማራጭ ባይሆንም የሕግ የበላይነትን የማስከበር ግዴታ ስላለበት በነዚህ አካላት ላይ የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እንገኛለን። እነዚህንና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን በመሥራታችን ነው በአጭ ጊዜ ውስጥ ውጤታማ ልንሆን የቻልነው።*

**ከባለድርሻ አካላት ጋር እንዴት ነው በቅንጅት እየሠራችሁ ያላችሁት?**

*የዕቅድ ስኬት ሊመጣ የሚችለው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሲሠራ ነው። ይህን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ከአምስት ክፍለ-ከተሞች የገቢ ጽ/ቤቶች፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ ነን። ባለድርሻ አካለቱም ከእኛ ጋር ለመሥራት ፈቃደኞች መሆናናቸው ላገኘነው ውጤት ትልቅ አቅም ሆኖልናል።*

**የታቀደላችሁን ዕቅድ ለማሳካት ከግብር ከፋዮች ምን ይጠበቃል?**

*ዕቅዱን ለማሳካት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሠራተኞች ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ ከግብር ከፋዮች የሚጠበቀው ግብርን በወቅቱ ማሳወቅ እና መክፈል ነው። ግብር ከፋዮች የሚከፍሉት ግብር ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ሀገራቸውን እና ሕዝብን እንደሚጠቅም አውቀው ለግብር ግዴታ ተገዢ መሆን አለባቸው። መክፈል ደግሞ በወቅቱ እና በትክክለኛ መጠን መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል። ምክንያቱም፤ ከዚህ ውጪ ሲሆን ትርፉ ለቅጣት መዳረግ ስለሆነ።*

*እንዲሁም፤ በሕጋዊነት መሥራት የሚያስመሰግን መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሕገ-ወጥ አካሔድ የሚታይባቸውን ደግሞ በመጠቆም ትብብራቸውን እንዲያሳዩ እጠይቃለሁኝ። ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እንዲደራጅ እና ሥራውን እንዲጀምር ከሠራተኞች በተጨማሪ ግብር ከፋዮች ያሳዩት እገዛ በአጭር ጊዜ ለተመዘገበው አመርቂ ውጤት አስተዋጽኦው ቀላል አልነበረም። ይህ የመተጋገዝ መንፈስ በቀጣይ ጊዜም እንዲቀጥል እያስገነዘብሁ የአሠራር ግድፈት ሲገጥም በግልጽ ቀርቦ ቅሬታን ማቅረብ እንደሚቻል ሳመለከት እኛም ለመታረም ዝግጁ መሆናችንን በማሳወቅ ነው።*



ገነት ሆቴል ፊት ለፊት የሚገኘው የመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቁጥር ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፤

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ፡- ሰሎሞን ወርቁ

# የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምና ድጋፍ አገልግሎት

1. **የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አቅራቢነት እውቅና ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የንግድ ዋና ምዝገባና ፈቃድ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- የሰለጠነ የሰው ኃይል አደረጃጀት (ሥራ አስኪያጅ፣ የጥገና ኃላፊ፣ ቴክኒሽያን፣ የሽያጭ ሠራተኛ፣ የመሳሪያ ተቀባይ፣ መሳሪያ አስረካቢ፣ ስልጠና ሰጪ፣ ኦፕሬተር)፤
- የቢሮ፣ ለስልጠና እና ለጥገና የሚሆን የተደራጀ ቦታ፤
- የአንድ ሚሊዮን ብር ዋስትና፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

2. **የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እውቅና ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የመሳሪያው ሁለት ናሙና እና ሌሎች መረጃዎች አደራጅቶ ማቅረብ፤
- ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምህንድስና አካል ውል መዋዋል፤
- የማስፈተሻ አገልግሎት ክፍያ መፈፀም፤
- ስለመሳሪያው በደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 9፣ 10 እና 11 መሰረት ዕውቅና የሚጠየቅበትን መሳሪያ ባህሪያት የሚያሳዩ ደጋፊ መረጃዎች ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

3. **የሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር አምራችና አከፋፋይ እውቅና ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት፤
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- የሰለጠነ የሰው ኃይል አደረጃጀት (ሥራ አስኪያጅ፣ ሶፍትዌር ዲቨሎፐር፣ ስልጠና ሰጪ፣ ኦፕሬተር) የማሟላት፤
- ለስልጠና እና ለጥገና የሚሆን የተደራጀ ቢሮ እና ቦታ፤
- የአንድ ሚሊዮን ብር ዋስትና የምስክር ወረቀት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

4. **ለሽያጭ ነቁጣ ሶፍትዌር እውቅና ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ሶፍትዌሩ የሚሠራበት ሶፍት ኮፒ እና ሌሎች ዶክመንቶች አደራጅቶ ማቅረብ፤
- ከፈታሽ አካል ውል መዋዋል፤
- የማስፈተሻ አገልግሎት ክፍያ መፈጸም፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት







**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

5. **የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ እና ሶፍትዌር አቅራቢነት እውቅና ስረዛ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 አንቀጽ 15 መሰረት የተዘረዘረ መረጃ ማቅረብ፤
- የእውቅና ሰርቲፊኬት የተሰጠው ሰው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 139/1999 ድንጋጌዎችን ተላልፎ መገኘት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምና ድጋፍ አገልግሎት

6. **የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ንግድ ፈቃድ፣ ዋና ምዝገባ፤
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፍኬት (ተመዝጋቢ ከሆኑ)፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና



7. **ዓመታዊ ዕድሳት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- በጽሑፍ ወይም በOnline ማስታወቅ፤
- ማሽኑን ወደ አገልግሎት ማዕከል ማስገባት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

8. **የማሽን አድራሻ ለውጥ ለማድረግ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የአዲሱ አድራሻ ንግድ ፈቃድ፣ ዋና ምዝገባ፤
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርቲፊኬት (ተመዝጋቢ ከሆኑ)፤
- ለአቅራቢው የተዘጋጀ ደብዳቤ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

9. **የማሽን የባለቤትነት፣ የስም እና የንግድ ስያሜ ለውጥ ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ባለቤትነት የሚያዞረው ፈቃድ ስለመመለሱ ማስረጃ ማቅረብ፤
- የባለቤት ለውጡን የሚወስደው ንግድ ፈቃድ፣ ዋና ምዝገባ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፍኬት (ተመዝጋቢ ከሆኑ)፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

10. **የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተመላሽ ለማድረግ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የንግድ ፈቃድ፣ ምዝገባው የተቋረጠበት ደብዳቤ፤
- የመጨረሻ ዜድ ሪፖርት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

11. **ተንቀሳቃሽ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ለማድረግ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ተንቀሳቃሽ ከተፈቀደላቸው የንግድ ዘርፎች ውስጥ መሆኑ፤
- የንግድ ዋና ምዝገባና ፈቃድ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

12. **በአደራ ለማስቀመጥ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የኪራይ ውል የተቋረጠበት፤
- በልማት ምክንያት የደረሰ ከሆነ ከሚመለከተው የተጻፈ ደብዳቤ፤
- በኦዲት (በአወሳሰን) ጊዜ ላይ መሆናቸው፣ በፍርድ ቤት ጉዳይ፣ በቅሬታ፣ በይግባኝ ወ.ዘ.ተ ላይ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ፤
- ዋና ምዝገባና የንግድ ፈቃድ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

13. **ከሲስተም ውስጥ ያለው የግብር ከፋይ መረጃ ተሳስቶ ማስተካከያ ሲጠየቅ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ማሽኑ ሲገዛ የነበረ መረጃ፤
- ሰርቪስ ቡክ፤
- ከማሽን የሚወጣው ዜድ ሪፖርት፤
- የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ዋና ምዝገባ፤
- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፤

አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

14. **ኤግዚቢሽን ላይ ለመሳተፍ ተንቀሳቃሽ ማሽን ለመጠቀም መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ከአዘጋጁ ባዛሩ ላይ እንደሚሳተፍ የሚገልጽ ደብዳቤ፤
- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት፣ ዋና ምዝገባ፣ ንግድ ፈቃድ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ የምስክር ወረቀት (ተንቀሳቃሽ ከተፈቀደላቸው)፤

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

# በየዓይነቱ

አዘጋጅ፡- እታገኝ አቦሰጥ

## የወራት ስያሜ እና ትርጉማቸው

ዳዊት ከበደ ወየሳ

በኢትዮጵያ የምንጠቀምባቸው የወራት ስሞች የአማርኛው መነሻ (ሥርወ) ቃል የተወሰደው ከግዕዝ ሲሆን ከግሪክም የተወሰደ አለ። ኦሮምኛም የወራቱን ስሞች በራሱ ቋንቋ የሚጠራ ሲሆን በተለያዩ የኦሮሚያ ቦታዎች ወራቱ በተለያየ ስያሜ ይጠራሉ። ለኦሮሚኛ እነዚህን ልዩ ልዩ ስያሜዎች ወደ አንድ መደበኛ ቃል ማምጣት በማስፈለጉ ከተለያዩ ቦታዎች በመሰብሰብ የተሻለውን እና በብዙዎች ዘንድ ጥቅም ላይ የዋለውን ቃል መርጦ በመደበኛ የኦሮምኛ ቃል ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል።

**በዚህም መሠረት**

- መስከረም «ፉልባና» ሲባል ስያሜውን ያገኘው ከሜጫ ኦሮሞ ነው።
- «አንኮሎሌሳ» የተባለው ጥቅምት ከአርሲ እና ከባሌ ኦሮሞ የተወሰደ ነው።
- ኅዳር ሦስተኛ ወር ነውና አርሲ እና ባሌዎች «ሰዳሳ» ስለሚሉት ቃሉ ከዚያ ተወስዷል።
- ታኅሣሥ በቱለማ ኦሮሞዎች ዘንድ «ሙዴ» ይባላል።
- ጥር «አማጂ» ማለት ሲሆን ስያሜውን ከአርሲ እና ከባሌ ኦሮሞ ነው ያገኘው።
- «ጉራንዳላ» ከቦረና ኦሮሞ የተወሰደ ሲሆን የካቲት ማለት ነው።
- ስያሜውን ከአርሲና ከባሌ ያገኘው «ቢቶሴሳ» መጋቢትን ይወክላል።
- ሚያዝያ «ኤልባ» የተባለው ቃሉን ከቱለማ ኦሮሞ ወስዶ ነው።
- ከግንቦት ጀምሮ ያሉት ወራት በአርሲ፣ በባሌ፣ በቦረና፣ በጉጂ እና በቱለማ ተመሳሳይ ትርጉም ስላላቸው ያለምንም ምርጫ ግንቦት «ጫምሳ»፣ ሰኔ «ዋጋባጂ»፣ ሐምሌ «አዶሌሳ» እና ነሐሴ «ሃጋያ» ይባላሉ።

ከነዚህ ወራት መካከል «ሳደሳ»፣ «አርፋሳ»፣ «አንኮሌሳ» እና «አዶሌሳ» ከኦሮምኛ በተጨማሪ በሲዳማም ለተመሳሳይ ወር ይጠቀማል።

**በአማርኛ ስያሜ በኩል**

- መስከረም፡- አበቦች በየመስኩ የሚፈነዱበትን እና አደይ አበባ ምድሪቱን የሚያለብስበት ወር ነውና ሮማውያን «መስከ-ሮም» ብለው ይጠሩታል። ይህን ቃል ጉራጌዎች «መስከሮም» ወይም «መስከሮብ» ይሉታል። አማርኛው ታዲያ ቃሉን ከርክሞ እና አስተካክሎ «መስከረም» ብሎታል።
- ጥቅምት፡- በተለይ በገበሬው ዘንድ ይህ ወር የሚታወቀው ጥራጥሬ ተዘርቶ እሸት በማፍሪያው ነው። ወሩ ከሌሎቹ በበለጠ ለገበሬው እና ለከብቶቹ ጠቃሚ በመሆኑ «ጠቃሚት» ወይም «ጥቅምት» ተብሎ ይጠራል።
- ኅዳር፡- አንዳንዶች ወሩን «ኅዳር» ከሚለው የግዕዝ ቃል ጋር በማዛመድ "ከማደር" ጋር ያያይዙታል። ወሩ በግብጽ እና በዐረብ አገሮች «አቶር» እና «ሃቶር» ሲባል በእብራይጥ ደግሞ «አዳር» በሚል ይታወቃል። በቸሃ ጉራጌ ይህ ወር «ይዳር» ይባላል።
- ታኅሣሥ፡- በግዕዝ «ኀሠሠ» ሲሆን «ተጓዘ»፣ «ሄደ» ወይም «አሠሠ» እንደማለት ነው። ወሩ፤ ወታደሩም፣ ነጋዴውም ከአገር ወደ አገር የሚንቀሳቀስበት፣ የሚሄድበት፣ አገር የሚያሥሥበት ነው። «ጉዞ» ለሚለው «ተጓዘ» እንደሚባለው «ኀሠሠ» ብሎ «ተኀሠሠ» በመሆኑ የጉዞ ወቅትነቱን ለማመልከት ቃሉ «ታኅሣሥ» ሆኗል።
- ጥር፡- በግዕዝ «ጥሁር» ወይም «ንጹህ» ወይም «ጥሩ» ማለት ነው። ጥር ሰብል ተሰብስቦ ጥጋብ የሚመጣበት፤ ሠርግ እና ምላሽ፣ ድግስ እና ግብዣ የሚዘወተርበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በጥንታዊው ደቡብ ዐረቢያ «ፀረረ» ሲባል በጉራጊኛ «ጥርር» በሚል ስያሜ ይጠሩታል። የዚህ መነሻ በወሩ ያለው ጠራራ ጸሐይ ሊሆን ይችላል።
- የካቲት፡- በግዕዝ «ከቲት» ወይም «ይከትት» ሲባል «መከተት» ከሚለው የአማርኛ ቃል ጋር አቻ ናቸው። ይህ ወር በገበሬው ዘንድ እህል ተሰብስቦ ወደ ጎተራ የሚከተትበት (መከተቻ) መሆኑን ለማመልከት «የካቲት» ተብሏል። «ከቲት» ማለት «ከታች» ሲሆን፤ «የካቲት» ደግሞ «የመከተቻ ጊዜ» እንደማለት ነው።
- መጋቢት፡- በግዕዝ ምግብ የሚመግብን ወንድ «መጋቢ»፤ መጋቢዋ ሴት ከሆነች ደግሞ «መጋቢት» ይባላል። በዚህ የበልግ ወር እህል እና ጥራጥሬ ብቻ ሳይሆን ወፍ ዘራሽ እና የጫካ ፍራፍሬዎች ጭምር በየስፍራው ያድጋሉ። እንሰሳት እና አእዋፋትም እንደልባቸው እና እንደሆዳቸው መጠን የሚመገቡበት ወር ስለሆነ ይህን የምግብ እና የጥጋብ ወር «መጋቢ» ወይም «መጋቢት» ብለው ጠሩት።
- ሚያዝያ፡- በዐረብኛ «ማዛ» ማለት «መልካም» ወይም «ጥሩ መዓዛ ያለው ሽታ» ማለት ነው። አንዳንድ ሰዎች ሚያዝያን ከመልካም ሽታ ጋር ያያይዙታል። ሚያዝያ የሚለው ቃል የሚወለደው «መሐዘ» ከሚለው የግዕዝ ቃል ሲሆን «ጎለመሰ» ወይም «ሚስት ለመያዝ በቃ» ማለት ነው። እንደልማድ ሆኖ ከግንቦት ወር ጀምሮ ሠርግ አይደረግም። ስለዚህ የጎለመሰ ወይም የመሐዘ ሰው ሚዜ አደራጅቶ ሚስት የሚያገባው ከግንቦት ቀድሞ በሚገኘው ወር ነው። በዚህ ምክንያት ወሩ «ትዳር መያዣ» ወይም «መሐዘ»፣ «መሐዘያ» ወይም «መያዣ» ሲባል ቆይቶ አማርኛው «ሚያዝያ» በማለት ቃሉን ወረሰው።
- ግንቦት፡- ትርጉም እና አመጣጡ አማርኛ ነው። በዚህ ወር መሰረት ተቆፍሮ ግንባታ የሚጀመርበት ነው። ለምሳሌ፡- «ፈለገ» ለሚለው «ፍላጎት» እና «ሰረቀ» ብሎ «ስርቆት» እንደሚባለው «ገነባ» ብሎ «ግንቦት» ይሆናል። በአገራችንም በዚህ ወር በርካታ የግንባታ ሥራዎች ይከናወናሉ። አጋጣሚ ይሁን ሆን ተብሎ ባይታወቅም የሕዳሴ ግድብ ግንባታ የተጀመረው በግንቦት ነው።
- ሰኔ፡- የቃሉ ምንጭ ትግረ ወይም ትግሪኛ ሲሆን «ሰነየ» ማለት «መልካም ሆነ»፣ «ሰናይ ሆነ»፣ «አማረ» ማለት ነው። ይህ ወር በአርጎብኛ፣ «ሰነይ» ይባላል። አማርኛው በሂደት ቃሉን ከ«ሰነይ» ወደ «ሰኔ» ቀየረና የዚህ ወር መጠሪያ አድርጎታል።
- ሐምሌ፡- በሐምሌ ክረምት ይገባና ልምላሜ ይጀምራል። የለመለመ ነገር ደግሞ «ሐመልማል» ይባላል። «ሐመለ» ማለት አበባ አፈራ ማለት ሳይሆን «አበበ» ወይም «ለመለመ» ማለት ነው። «ሐምለይ» ማለት ደግሞ «ለምለም» ማለት ነው። በሥነ-ቃል ብዜት «ሐመለ፣ ሐምለይ፣...» እያለ ይበዛል። ደቡብ አርጎባም ቢሆን እንደ አማርኛ ወሩን «ሐምሌ» ነው የሚለው። ወሩ በትግሪኛ «ሐምለ»፤ በክስታኔ፣ በስልጢ፣ በወለኔ እና ሙኸር ሐምሌን «አምሌ» ይሉታል።
- ነሐሴ፡- በግዕዝ «ነሐሰ» ማለት መሥራት ወይም መገንባት ነው። በአገራችን በነሐሴ ወር የሚገነባ ነገር ብዙም ስለሌለ ቃሉ ከግዕዝ መጣ ለማለት ያስቸግራል። የዚህ ወር ትክክለኛ አመጣጥ ሊሆን የሚችለው በሰማይ ላይ የምናያቸው ነሐሳማ ቀለማት ናቸው።

ነሐስ በባህሪው እየቆየ ሲመጣ ቀለሙ ወደግራጫነት ይቀየራል። የነሐሴን ሰማይ ብንመለት እንደ አህያ ሆድ ነጣ፣ ገርጠት እና ጠቆር ብሎ እናየዋለን። እናም የነሐሴ ወር ሰማይ ነሐስ የመሰለ፣ ነሐሰይ የሆነ ነው። «ነሐሰይ» ማለት ደግሞ ነሐስማ ቀለም ማለት ሲሆን አማርኛው ደግሞ ልክ «ሰነይ»ን ሰኔ እና «ሐምለይ»ን ሐምሌ እንዳለው፤ «ነሐሰይ»ን ነሐሴ ብሎታል።

ጳጉሜ፡- ቃሉ ከግሪክ የተወሰደ ሲሆን የኢትዮጵያ 12 ወራት ወይም 360 ቀናት ካለቁ በኋላ ሽርፍራፊ እና ቀሪ አምስት ወይም በአራት ዓመት አንዴ ስድስት ቀናት ይኖራሉ። እነዚህ ትርፍራፊ ቀናት በእንግሊዝኛው «Epagomenal» ይባላሉ። በግሪክ ደግሞ «ፓጉሜን» ይሉታል፤ የግሪክ አቻ ትርጉሙ «የተረሱ ቀናት» ማለት ነው። ኢትዮጵያውያን ደግሞ እነዚህን ቀናት በአንድ መድበው 13ኛ ወር አድርገውታል።

«ኅብረ አትዮጵያ» የተሰኘው የቴዎድሮስ በየነ ጽሑፍ ደግሞ ለየወራቱ ቀጣዮቹን ትርጓሜ አስቀምጧል።

**መስከረም**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «መስ» እና «ከረም» ሲሆን «መስ» - «አለፈ»ን እና «ከረም» - «ክረምት» የሚለውን ትርጉም አምጥቶ «ክረምት አለፈን» ይተካል።

**ጥቅምት**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ጠቀመ» ሆኖ ትርጉሙ «ሠራ»፣ «ጠቃሚ ጊዜ» ይሆናል።

**ኅዳር**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ኀደረ» ሲሆን ትርጉሙ «አደረ» ብሎ ሰው በአዝመራ ወር ማሳ ውስጥ ለጥበቃ ማደሩን ይገልጻል።

**ታኅሣሥ**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ኀሠሠ» ሆኖ ትርጉሙ «መረመረ» በመሆን በመኸር ወቅት የሰብል ምርመራን ያመለክታል።

**ጥር**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ነጠረ» ሲሆን ትርጉሙ «ጠረረ»ን፣ «ብልጭ አለ»ን እና «ነጻ»ን አመልክቶ የፀሐይ ግለት ወቅትነቱን ያሳያል።

**የካቲት**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ከቲት» ሆኖ ትርጉሙ «መከተቻ» በመሆን የዕህል መከተቻ ወይም ወደ ጎተራ መግቢያን ያመለክታል።

**መጋቢት**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «መገበ» ሲሆን ትርጉሙ «በቁሙ የሚመግብ»ን አመልክቶ በጎተራ የተከተተው የሚበላበት ወርነቱን ያሳያል።

**ሚያዝያ**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «መሐዘ» ሆኖ ትርጉሙ «ጎለመሰ»፣ «ጎበዘ»፣ «ሚስት ፈለገ» ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው ወሩ የሠርግ መሆኑን ነው።

**ግንቦት**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ገነበ» ሲሆን ትርጉሙ «ገነባ»፣ «ሠራ»፣ «ቆፈረ»፣ «ሰረሰረ» ሲሆን መሬቱ ለእርሻ መዘጋጀቱን ያሳያል።

**ሰኔ**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ሰነየ» ሆኖ ትርጉሙን «አማረ» በማለት የአዝርዕቱን መዘራት ያመለክታል።

**ሐምሌ**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «ሐመለ» ሆኖ ትርጉሙ «ለቀመ» ሆኖ የጎመን መለቀሚያ ወይም መሰብሰቢያ ወርነቱን ያሳያል።

**ነሐሴ**

- የግእዝ ሥርወ-ቃሉ «አናሕስየ» ሆኖ ትርጉሙ «አቀለለ»፣ «ተወ» በማለት ክረምቱ እያደር መቅለሉን ያመለክታል።

**ጳጉሜ**

- የግሪክ ሥርወ-ቃሉ «ኤጳጉሚኖስ» ሲሆን ትርጉሙ «ተጨማሪ» ማለት ነው።

## በኢትዮጵያውያን መዋጮ የተሠራው ሆስፒታል

በአጼ ኃ/ሥላሴ የንግሥና ዘመን፣ «የልዑል መኮንን መታሰቢያ» እየተባለ ይጠራ የነበረው እና በዚህ ስያሜ እስከ 1968 ዓ.ም. የቀጠለው ሆስፒታል በደርግ የአገዛዝ ዘመን «ጥቁር አንበሳ» ተብሎ እስካሁን በዚያው ይጠራል። በሕዝብ መዋጮ የተሠራው ሆስፒታሉ ግንባታው በ1954 ዓ.ም. ተጀምሮ በ1964 ዓ.ም. ነበር የተጠናቀቀው።

በአዲስ ዘመን ጋዜጣ 21ኛ ዓመት ቁጥር 259 የቅዳሜ ጥቅምት 25/1954 ዓ.ም. ዕትም መረጃ መሠረት ለሆስፒታሉ መገንቢያ የዋለውን 4 ሚሊዮን 891ሺ 167.14 ብር ከሕዝብ እና ወዳጅ ከሆኑ የውጭ ሀገር ሰዎች ተዋጥቷል። በዚህም መሠረት፡-

- የአዲስ አበባ ነዋሪ እና የመንግሥት ሠራተኞች፡- 2 ሚሊየን 436ሺ 515.64
- ከኤርትራ፡- 302ሺ 557.25
- ከሐረር፡- 252ሺ 862.53
- ከሸዋ፡- 238ሺ 909.05
- ከሲዳሞ፡- 208ሺ 632.60
- ከከፋ፡- 188ሺ 898.00
- ከወለጋ፡- 128ሺ 182.77
- ከኢሉባቦር፡- 118ሺ 017.22
- ከበጌምድር እና ከስሜን፡- 107ሺ 631
- ከትግራይ፡- 104ሺ 100
- ከአርሲ፡- 18ሺ 626
- ከጎጃም፡- 92ሺ 863
- ከጋሞ ጎፋ፡- 59ሺ 400
- ከባሌ፡- 47ሺ 328.50 ብር አዋጥተው ነበር።

በዚያን ጊዜ ለ20 ሚሊዮን ሕዝብ እንዲያገለግል የተሠራው ይህ ሆስፒታል ዛሬ ለ120 ሚሊዮን ሕዝብ በስፔሻላይዝድ ሪፈራልነት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።



# የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አጠቃቀምና...

ከገጽ 2 የዞረ

- የማሽን ቁጥር (MRC No)፤
- ብልሽቱ ወይም ችግር የንግድ አድራሻ እና ልዩ ቦታ፣ ቀንና ሰዓት ማስመዝገብ፤
- የእጅ በእጅ ደረሰኝ የጀመረበትን መነሻ ቁጥር ማስመዝገብ፤
- የእጅ በእጅ ደረሰኝ ያቆመበትን ቁጥር እና ማሽኑ ሥራ የጀመረበትን ሰዓትና ቀን ማስታወቅ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**20. ለኦዲት/ለአወሳሰን የእጅ በእጅ ደረሰኝ መጠቀም ወይም Z-report ያልወጣበት ምክንያት ለማስታወቅ**

- በወቅቱ ችግሩን ያስመዘገበ መሆኑን ማስታወቅ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**21. መብራት መጥፋት ወይም ብልሽት በወቅቱ ሳያስመዘግቡ ለመስተናገድ የአገልግሎት ጥያቄ**

- እድሳት እና ብልሽት ከሆነ በሰርቪስ ቡክ የተመዘገበበትን ማቅረብ፤
- መብራት መጥፋት ከሆነ ቃለ-መሃላ መግባት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**22. ለጥገና ወይም ዓመታዊ ዕድሳት የገባ ማሽን መመለሱን ለማስታወቅ**

- በጽሑፍ ወይም በonline ማስታወቅ፤
- የምርመራ መዝገብ ማቅረብ፤
- ማሽኑ ወደ አገልግሎት ማዕከል ሲገባ ያስመዘገቡበትን የመዝገብ ቁጥር ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**23. የተሰረቁ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማስታወቅ**

- ማሽኑ መጥፋቱን ከፖሊስ ጣቢያ ማስረጃ ማቅረብ፤
- ማሽኑ ከመጥፋቱ በፊት የነበረ የመጨረሻ ቀን ዜድ ሪፖርት ማቅረብ፤

**አገልግሎት የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**24. በማሽን ላይ ሚሞሪ ሲቀየር በማስታወሻ ላይ ያልተመዘገበ ሽያጭ ከኦርጂናል ተናቦ ይሠራልኝ ጥያቄ**

- ከአቅራቢው ከዋናው መሥሪያ ቤት በማሽን ማስታወሻ ላይ ያልተመዘገቡ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ፤
- ኦርጂናል ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**25. መረጃ ተቀበለኝ የአገልግሎት ጥያቄ**

- የግዥና ሽያጭ ቅፆች ሞልቶ ማቅረብ፤
- በTIN እና ያለTIN የተፈፀሙ ግዥዎችን ለይቶ ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**26. የንግድ ፈቃድ ለመዝጋት መረጃ ይጣራልኝ ጥያቄ፣**

- ድርጅትን ለመዝጋት የተያዘ ቃለ-ጉባዔ፤
- የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ሰርቲፊኬት ኮፒ፤
- ለከብት ዕርድ አገልግሎት መረጃ ፈላጊዎች የዕርድ መስመርና የመስመር ቁጥር፤
- ለግሮሰሪ፣ ለሆቴል፣ ለባርና ሬስቶራንት፣ የቢራ፣ የድራፍት፣ የለስላሳ እና አልኮል መጠጥ ወኪል አከፋፋይ ካርድ ፍቶ ኮፒ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**27. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ስተፈጠረ ስህተት ተመላሽ ለመጠየቅ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ፤
- በስህተት የተቆረጠው ደረሰኝ ኦሪጅናል፤
- ተስተካክሎ የተቆረጠው ደረሰኝ ኮፒ፤
- በስህተት የተቆረጠው ደረሰኝ ኦርጅናል፤
- ተስተካክሎ የተቆረጠው ደረሰኝ ኦርጅናል፤
- የቀን Z ሪፖርት፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**28. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ኦርጅናል መቀጥቀጥ ሲኖር አገልግሎት ለማግኘት**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፍርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን አገልግሎቱን ለማግኘት በታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት ክፍል ነው።

**29. በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የተዘለለ መረጃ ሲኖር /Reset/ ማስተካከያ ለማድረግ ሲያስፈልግ**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰጥበት የሥራ ክፍል የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት ነው።

**30. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ሲል /ማሽጊያ/ መልቀቅ ሲኖር ለማስተካከል**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት ነው።

**31. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ማስተር ቦርድ መቃጠል** EJ /ኤሌክትሮኒክ ኦርጅናል/ መጨረሻ አለመገኘት ሲኖር

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት ነው።

**32. ማሽኑ ላይ የቀን ወደኋላ ወይም ወደፊት መሄድ (የቀን መዛባት ሲኖር) ለማስተካከል**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት ነው።

**33. መረጃ ልከው ማረጋገጫ ያልወጣላቸው ማሽኖች እንዲዘጉልን /48 ሰዓት ያስፈባቸው/ አገልግሎት ለማግኘት**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት አገልግሎቱን ይሰጣል።

**34. FM ለውጥ፣ FM መዘባረቅ፣ የEJ /ኤሌክትሮኒክ ኦርጅናል ችግር ያለበት ለማስተካከል**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት አገልግሎቱን ይሰጣል።

**35. የኦርጅናል መጥፋት /ኦርጅናል ያለመገኘት/ አገልግሎት ለማግኘት**

የድርጅቱ ማህተም ያለበት ማመልከቻ ወይም የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ሞልቶ ማቅረብ ሲሆን የታክስ መረጃና የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አስተዳደር የሥራ ሂደት አግልግሎቱን ይሰጣል።

**36. የሀገር ውስጥ ግዢ እና ሽያጭ መረጃ፣ በመረጃ መረብ ለመላክ ሲያስፈልግ**

በ Ministry of Revenues ዌብሳይት ላይ ገብተው መመዝገብ ይቻላል። እንዲሁም አካውንት እንዲከፈትላቸው የተመዘገቡትን ሠራተኞች ዝርዝር በደብዳቤ ማሳወቅ።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና።

**37. መረጃ ይጣራልኝ የአገልግሎት ጥያቄ**

- ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የተጻፈ ደብዳቤ፤
- የንግድ ፈቃድ ኮፒ፤
- የግብር ከፋይ መለያ የምስክር ወረቀት ኮፒ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ መረጃ እና የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**38. ከአምራችና አከፋፋይ ድርጅቶች የሚሰበሰብ የሽያጭ መረጃ በማጠናቀር እና በመተንተን ለክልሎች ማሰራጨት አገልግሎት ለመስጠት**

ለክልሎች የአገልግሎት መጠየቂያ ፎርም ወይም ደብዳቤ ማቅረብ ይገባል።

# ለሚ’ገባው ይግባ!

ከገጽ 8 የዞረ

ያልወጣ እና እንደ ሕግ የአስገዳጅነት ኃይል የሌለው በመሆኑ ላቀረበው ጉዳይ አግባብነት የለውም ተብሎ ውድቅ ተደርጓል።

ዋናው ጉዳይን በተመለከተ ከግራ ቀኙ ክርክር ይዘት በግልጽ መረዳት የሚቻለው አመልካች በ2008 ዓ.ም የበጀት ዓመት ያገኘው የተጣራ ትርፍ ለድርጅቱ ካፒታል ማሳደጊያነት ስለመዋል አለመዋሉ ነው። በመመሪያው ያልተከፈለ ትርፍ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ከግብር ነጻ የሚሆነው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ እንደሆነ፤ ከግብር ነጻ ለመሆንም መቅረብ ስለሚገባቸው የማስረጃ ዓይነቶች በዝርዝር ተመልክቷል።

በዚህ አግባብ ያልተከፈለ ትርፍ ማለት የድርጅቱ የሂሳብ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉት 12 ወራት ውስጥ ለባለአክሲዮኖች ያልተከፈለ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ባቋቋመው በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት አማካኝነት የንግድ ሥራ ለሚያካሂድ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት ያልተላከ ትርፍ ወይም የኩባንያው ካፒታል ለማሳደግ ያልዋለ የተጣራ ትርፍ ማለት እንደሆነ በመመሪያው አንቀጽ 3/1/ ስር ተመልክቷል። በዚህ መልኩ የተገኘው ትርፍ ከግብር ነጻ የሚሆነው ደግሞ የተጠቀሰው የድርጅቱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ 12 ወራት ውስጥ የአባላቱን የአክሲዮን ድርሻ መጠን እና የድርጅቱን ካፒታል በተገኘው የተጣራ ትርፍ መጠን አሳድጎ ሲገኝ እንደሆነ በመመሪያው አንቀጽ 5/2/ ስር ተመልክቷል። ይህንን ለማስረዳትም በሰነዶች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ወይም አግባብነት ባለው የክልል /የከተማ አስተዳደር ቢሮ የጸደቀ የድርጅቱ ቃለ-ጉባኤ እና ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም አግባብነት ባለው አካል/ንግድ ቢሮ የድርጅቱ ካፒታል ስለማደጉ የሚገልጽ ሰነድ በመመሪያው በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቅረብ እንደሚገባው በመመሪያው አንቀጽ 6/1/እና 7 ስር ተመልክቷል።

ከዚህ የመመሪያው ዝርዝር ይዘት መረዳት እንደሚቻለው በአንድ የግብር ዘመን የተገኘ የድርጅት የተጣራ ትርፍ ከግብር ነጻ የሚሆነው የተገኘው ትርፍ ለባለአክሲዮኖቹ ሳይከፋፈል ለኩባንያው ካፒታል ማሰደጊያት የዋለ እንደሆነ እና የኩባንያው የካፒታል መጠን በበጀት ዓመቱ በተገኘው ትርፍ ልክ ያደገ ስለመሆኑ በመመሪያው በተመለከተው የማስረጃ ዓይነት ማረጋገጥ የተቻለ እንዲሆን ብቻ ነው።

በመሆኑም ሰበር ፍርድ ቤት የመ.ቁ. 214263 መጋቢት 27/2015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ አመልካች “ፀሐይ ኢንዱስትሪ አክሲዮን ማህበር” በ2008 በጀት ዓመት ባገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ ግብር እንዲከፍል በተጠሪ “የገቢዎች ሚኒስቴር” መጠየቁ እና መወሰኑ፤ በየደረጃው ያሉት መደበኛ ፍርድ ቤቶችም ይህንኑ በመቀበላቸው የፈጸሙት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ከዓመታዊው የተጣራ ትርፍ ላይ 10 በመቶ እንዲከፈሉ ሲል ውሳኔውን አጽንቶታል።

# Tips

BY SHIMELIS SISAY

## The World Bank's initiatives to modernize tax administration boost tax collection



*World bank country director Mr. Ousman Dine and Ethiopian revenues minister Mrs. Aynalem Nigusie;*

The Ministry of Revenues has been utilizing a variety of technologies to collect the tax. Taxpayers, non-governmental groups, and international organizations must all contribute in order to accomplish this. Besides the Ministry's and the government's responsibilities, the active involvement of those bodies will play a pivotal role in modernizing the tax system.

The World Bank and the Minister of Revenues have discussed supporting Ethiopia to support its effort to modernize the tax system.

The discussion was focused on the application of project proposals to modernize the administration that would enable cost-effective and efficient service delivery.

In the discussion, it was pointed out that the project will have an optimistic impact on increasing the ratio of Ethiopia's tax revenue to the GDP. Generating Progressive ideas and supporting efforts to build an efficient, modern, and accessible tax administration system will be included in the project.

The Minister of Revenue, Mrs. Aynalem Niguse said that the project should be applied to the regions in addition to the federal consistently. The objectives of the project have to be aligned with Ethiopia's 10-year development plan and with the development and investment plan held in the middle ages.

In the design phase of the project, works to be done so far to modernize the tax system and other initiatives should be evaluated and included and the process has to focus on avoiding duplication of work and waste of resources according to her.

To develop the project design, it was stated that the Ministry of Revenue and the experts of the World Bank would conduct various studies in a short period of time

The World Bank country director Mr. Ousman Dione said that the World Bank is applying a long-term project to do several activities. Capable and Productive Civil Service, Modernizing and Digitizing Tax Administration to Leverage Technology and Data Analytics, bridging the tax and GDP, and Expanding sources of Taxation-Improving the Quality and Availability of Taxpayer Services are the major focuses of the project according to the director.

Finally, the director expressed his hope that the Ministry will give the necessary support for the preparation of the project to start its work.

## Live for others

- Rivers do not drink their own.
- Trees do not eat their own fruit.
- The sun does not shine on itself.
- Flowers do not spread their fragrance for themselves.
- We are all burned to help each other.
- Life is good when you are happy, but much better when others are happy because of you.
- Generally, living for others is a rule of nature.

Source: - From internet

By Adane Wubet

## Taxpayers Identification Number /TIN/ issuance

Taxpayers identity numbers will be given in order to identify the taxpayers. In accordance with the tax laws, the taxpayer must use the taxpayer identification number. The taxpayer's taxpayer identity number, which will be given to them at registration, cannot be more than one.

The mere possession of a taxpayer identification number certificate does not entitle the holder to the obligation to pay tax without the issuance of a legitimate trade license and the conduct of business.

Despite this, if a person gets revenue, they are obligated to pay tax, even if they do not have a valid trade license or taxpayer identity number certificate.

Each region or city government may provide a taxpayer identification number to a person who receives revenue by renting a home in more than one region or city administration.

If the taxpayer's certificate with their tax identification number is lost for any reason, they can acquire a replacement by presenting the tax authority oath, or if it is damaged, they can report it in writing and request a printed certificate with their original tax identity number.

## Regarding royalties

Payments made for any of the following are considered royalties:

A. The right to use any literature, artistic or cinematographic films that are in use for radio, television or Internet broadcasting;

B. To get the right to receive images, sounds or both, transmitted or displayed by satellite, cable, optic fiber or other similar technology in connection with television, radio or Internet broadcasting;

C. To get the right to use any patent, invention, trademark, design or model, plan, secret formula or process or other similar asset or right;

D. The right to use any industrial, commercial or scientific equipment;

E. Use or acquire the right to use information relating to any industrial, commercial or scientific experience;

F. Additional and supplementary support that enables to use of the resources or rights listed in alphabetical order (A-E); the payment will be made at one time or periodic.

## About Excise tax and record

Any person responsible for paying excise tax is obliged to keep and maintain records.

The record has to be

- prepared, printed or written in a legible and indelible manner, if change or correction is made before approval it must be clearly identified. The signature of the person who made the correction and the date of correction have to be written;
- Prepared in an authorized manner, electronically or otherwise and must not have been altered except in an authorized manner.

Any record or document that was not created in conformity with the decree or directive may be refused by the Ministry, Additionally, it could specify the format in which any financial reports must be delivered or the type of documents acceptable for execution.

# ሕገ-ግብር

አዘጋጅ:- ሰሎሞን ወርቁ

ይህ አምድ የታክስ አስተዳደርና የጉምሩክ አሠራር የሚመራበትን ህጐች፣ መመሪያዎችና አሰራሮች፣ ለሕግ ተገዢነት የሚያስተምሩ አስተሳሰቦችን፣ ሕጎችን ለአሠራር ምቹ የሚያደርጉና ፍትሃዊ የንግድ ውድድርን የሚያጎለብቱ አሰራሮችንና ተሞክሮዎችን የሚያስተዋውቅ ጽሑፍ ይቀርብበታል፡

## ለሚ’ገባው ይግባ!

በዚህ ርዕስ “ገ” እና “ባ” ፍደላት ጠበቅ ተደርገው እንዲነበቡ እየጠየቅን ‹‹የቄሳርን ለቄሳር፤ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር›› በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ መሠረት ነው ርዕሱን የሰጠነው።

ጅማሬው በ2008 ዓ.ም ሆኖ ለስምንት ዓመታት የተጓዘው የፍርድ ሒደት በመጋቢት 2015 ዓ.ም. እልባት አግኝቷል። ይህ ውሳኔ የመጨረሻ እና ይግባኝ የማይባልበት የሰበር ውሳኔ በመሆኑ ለሌሎችም አስተማሪ እና የሕግ አስገዳጅነት አለው።

የአሁኑ ተጠሪ በነገረ ፈጁ አቶ ወንድሙ አዲሴ አማካይነት ተወክሎ ቀርቧል። አመልካች ደግሞ በጠበቃ ብናልፍ ባሻ አማካኝነት ተወክሎ ቀርቧል። ተጠሪ አመልካችን በ2008 በጀት ዓመት ካገኘው የተጣራ የትርፍ ግብር እንዲከፍለው ጠይቋል። ምክንያት ያለውም አንድ ድርጅት በበጀት ዓመቱ ካገኘው የተጣራ ትርፍ በአንድ የግብር ዓመት ግብር ከተከፈለ በኋላ ለአባላቱ ያልተከፋፈለ እና መልሶ ኢንቨስት ያልተደረገ ከሆነ፤ ከተጣራ የድርጅቱ ትርፍ ላይ 10 በመቶ ግብር ይከፈልበታል። ይህንኑ አስመልክቶ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር (በአሁኑ ስያሜ የገንዘብ ሚኒስቴር) መመሪያ ማውጣት የሚችል ስለመሆኑ እንዲሁም የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 61 ይደነግጋል የሚለውን እና ቀድሞ ለተፈረመ የአክሲዮን ድርሻ እዳ ክፍያ የዋለ ትርፍ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 2/10/፣ 34 እና 60 መሰረት ለባለአክሲዮኑ እንደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም (ገቢ) የሚቆጠር በመሆኑ ግብር ሊከፈልበት የሚገባ ነው የሚለውን መሰረት በማድረግ ነው።

አመልካች በበኩሉ ህዳር 10/2009 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በበጀት ዓመቱ የተገኘው የተጣራ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ሆኖ በክፍፍሉም በ2004 ዓ.ም. በተደረጉ የደርጅቱ ካፒታል እድገት ውሳኔ መሰረት ለተፈረመ አክሲዮን ዕዳቸውን ከፍለው ላልጨረሱት ባለአክሲዮኖች ለአክሲዮን ግዥ እንዲውል፤ እዳው ለሌለበቸው ደግሞ እንዲከፋፈል ተወስኗል። በዚህ መሰረት ትርፉ ለካፒታል እድገት በመሆኑ ሊከፈልበት አይገባም ብሏል።

ተጠሪም አመልካች ያቀረበው መከራከሪያ እውነት ከሆነ እና ለድርጅቱ የካፒታል እድገት የዋለ ቢሆን በ2005 ዓ.ም በታደሰው የንግድ ፈቃድ ላይ የሚታይ የካፒታል እድገት መኖር ነበረበት። ነገር ግን በታደሰው ንግድ ፈቃድ ላይ የካፒታል እድገት የለም በማለት ተከራክሯል። አመልካችም ከዚህ ሌላ ያቀረበው ማስረጃ የለም። ይህንኑ ድንጋጌ መሰረት በማድረግም የገንዘብ ሚኒስቴር ባልተከፋለፈለ ትርፍ ላይ ስለጣለው ግብር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 7/2011 አውጥቷል ብሏል።

በዚህም መሰረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲሁም ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች በየደረጃቸው የተጣራ የትርፍ ግብር መክፈል የለብኝም በማለት ምክንያቱን አመልካች ከላይ በዘረዘረው መልኩ ቢገልጽም ይግባኙን ውድቅ አድርገውታል። ምክንያቱም ተጠሪ መሥሪያ ቤትም ሆነ በየደረጃው ያሉት የዳኝነት አካላት በትርፍ ላይ ግብር እንዲከፈል የወሰኑትም ከላይ የተነሱትን ጉዳዮች ተገንዝበው በመሆኑ ውሳኔው ተገቢ ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ ጉዳይ ሌሎች ግብር ከፋዮች ከግብር ነፃ ተደርገዋል በሚል አመልካችም ያቀረበው የመከራከሪያ ቅሬታ በሰበር ፍርድ ቤት በነበረው ክርክር ያልቀረበ በመሆኑ በዚህ ደረጃ ሊቀርብ አይገባም። ተሰጠ የተባለው ውሳኔም ቢሆን የህዝብ እና የመንግሥት ጥቅምን በእጅጉ የሚጎዳ መሆኑ ተረጋግጦ አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት ስህተቱ እንዲታረም ለሚኒስትሩ ቀርቦ በመታየት ላይ በመሆኑ ፍጻሜ ያገኘ ጉዳይ አይደለም። ጽ/ቤቱም ቢሆን የሚሰጠው ውሳኔ እንደየትኛውም የበታች ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚታይ በመሆኑ ችሎቱን የሚያስገድደው ባለመሆኑ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ውሳኔው ሊጸና ይገባል በሚል ተጠሪ የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል።

ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል።

አመልካች መስከረም 06/2015 ዓ.ም ባቀረበው አቤቱታ በዚህ ችሎት በመታየት ላይ ካለው ክርክር ጋር በተያያዘ ገንዘብ ሚኒስቴር ነሐሴ 11/2014 ዓ.ም የአመልካችን መከራከሪያ የሚደግፍ ሰርኩላር ያወጣ መሆኑን ጠቅሶ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ የተጠቀሰውን ሰርኩላር ከግንዛቤ እንዲያስገባለት ጠይቋል። ተጠሪ ደግሞ ታህሳስ 11/2015 ዓ.ም በተጻፈ መልስ ሰርኩላር ተብሎ የቀረበው ማስረጃ የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 የሚጥስ ነው የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲሁም ሚኒስትሩ ከስልጣን ውጭ ያወጡት በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም የሚልበትን ምክንያት ጠቅሶ ተከራክሯል።

ይኸው ጉዳይ በምርመራ ላይ እንዳለ የአሁን ተጠሪ የካቲት 27/2015 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ አመልካች የገንዘብ ሚኒስቴር ያወጣው ሰርኩላር ነው በማለት ያቀረበውን ደብዳቤ አስመልክቶ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤትን የሚያስከትሉ መልዕክት የያዙ ሕጋዊ ሰነዶችን በሰርኩላር መልክ ማውጣት ከፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ጋር የሚጋጭ መሆኑን ጠቅሶ መሰል ሰነዶች ካሉ በአዋጁ በተመለከተው አግባብ የመመሪያ አወጣጥ ሥርዓትን በተከተለ መልኩ እንዲፈጸም ለተጠሪ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ መሆኑን በመግለጽ ቀደም ሲል በአመመልካች የቀረበውን ሰነድ አስመልክቶ ካቀረበው መከራከሪያ አንጻር ይኸው በምርመራ ወቅት እንዲታይለት ጠይቋል።

ችሎቱም በግራ ቀኙ የቀረቡትን አቤቱታዎች እና አንዱ በሌላው አቤቱታ ላይ ያቀረባቸውን መከራከሪያዎች መርምሯል። በዚሁ መሰረት አመልካች ገንዘብ ሚኒስቴር ያወጣው ሰርኩላር ነው በማለት ከአቤቱታው ጋር ያቀረበው ሰነድ ለአሁን ተጠሪ መ/ቤት በቀጥታ የተጻፈ ደብዳቤ መሆኑን ከሚገልጽ በቀር አመልካች በገለጸው አኳኋን ሰርኩላር መሆኑን የሚገልጽ ነገር የለውም። የደብዳቤው ይዘት ሲታይም ለባለአክሲዮኖች ያልተከፋፈለ የንግድ ድርጅት ትርፍን አስመልክቶ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 61 ስር የተመለከተው ድንጋጌ ሲተረጎም የሚገባበትን አኳኋን የሚገልጽ ነው።

በሌላ በኩል የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ሥራ ላይ ከዋለበት መጋቢት 29/2012 ዓ.ም. ጀምሮ መመሪያን የማውጣት ስልጣን በተሰጣቸው በማናቸውም አስተዳደር አካላት የሚወጣው መመሪያ በአዋጁ አንቀጽ 7-10 ስር በተመለከተው አግባብ መውጣት ያለበት መሆኑን በአዋጁ አንቀጽ 4/2/ ስር ተመልክቷል። በአዋጁ መሰረት መመሪያ የሚባለው በሕግ አውጪ አካል በሚሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት በአስተዳደር ተቋም የሚወጣ እና በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ውጤት የሚያስከትል የሕግ ሰነድ ሲሆን በሥራ ላይ ያለ መመሪያን የሚያሻሽል ወይም የሚሽር የሕግ ሰነድንም የሚጨምር ስለመሆኑ በአንቀጽ 2/2/ ስር ተመልክቷል፡። በቅርጽ ደረጃም የሚወጣው መመሪያ የመመሪውን ተራ ቁጥር፣ መመሪያው እንዲወጣ የስልጣን ምንጭ የሆነውን ሕግ፣ የመመሪያውን አጭር ርዕስ፣ ትርጓሜ፣ የተፈጻሚነት ወሰን፣ ዋና ዋና ድንጋጌዎች፤ የማሻሻያ፣ መሻሪያ፣ መሸጋገሪያ እና ማቆያ ድንጋጌ ካለ ይህንኑ የሚመለከት ድንጋጌ እንዲሁም መመሪያው የወጣበትን እና ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን የያዘ መሆን እንደሚገባው በአዋጁ አንቀጽ 15 ስር ተመልክቷል።

ከዚህ አንጻር አመልካች ያቀረበው ሰነድ የፌደራል አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የተጻፈ ሲሆን በይዘትም ሆነ በቅርጽ ደረጃ የተጻፈ ደብዳቤ ነው ከሚባል በስተቀር የመመሪያ መልክም ሆነ መመሪያን ለማስፈጸም የወጣ አስገዳጅነት ያለው ዝርዝር ሕግ መልክ ያለው አይደለም። በመሆኑም የቀረበው ሰነድ በአዋጁ በተመለከተው አግባብ

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የኬንያው ፕሬዝዳንት የሀገራቸውን የግብር ሰብሳቢ ኤጀንሲ ወነጀሉ

የኬንያን ፕሬዝዳንት ዊልያም ሩቶ የሀገራቸውን የታክስ ሰብሳቢ ኤጀንሲ ሠራተኞች፣ "ለሀገራቸው ሳይሆን ከታክስ ሰዋሪዎች ጋር በመመሳጠር ሀገራችውን የሚያቆረቁዙ ወንጀለኞች ናቸው" ሲሉ ከስሰዋል፡፡

‹‹መመሳጠር፣ ዐይን ያወጣ ጉቦኝነት እና ስር የሰደደ ሙሰኝነት በኬንያ የግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ተንሰራፍቷል›› የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ‹‹ከዚህ ቀደም የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱን በማዘመን ግብር ከፋዮች በዲጂታል ቴክኖሎጂ የክፍያ ሥርዓት ክፍያ እንዲፈጽሙ ያደረግነው ጥረት በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት ሠራተኞች ደባ ሊመክን ችሏል›› ብለዋል፡፡




የኬንያ ፕሬዝዳንት ዊልያም ሩቶ፤

እ.ኤ.አ በ2019 የግብር ሰብሳቢ ኤጀንሲው 75 ሠራተኞች ከግብር ስወራ እና ጉቦ ከመቀበል ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለው እንደነበር ተነግሯል፡፡

እ.ኤ.አ በ2022 ነሐሴ ላይ ሀገሪቱን በፕሬዚዳንትነት እንዲመሩ የተመረጡት ሩቶ ከቀድሞው ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ስልጣን ሲረከቡ የሀገሪቷ የውጪ ዕዳ 34 በሊዮን ዶላር ነበር፡፡

የክፍያ ጊዜው የደረሰ የውጪ ዕዳ ክፍያ መጨመር፣ ለመሰብሰብ የታቀደው የገቢ ግብር ዝቅተኛ መሆን እና የመሠረታዊ ፍጆታዎች ዋጋ ማሻቀብ የኬንያን ኢኮኖሚ በፕሬዚዳንት ዊልያም ሩቶ አስተዳደር አንዳንገዳገደው ሮይተርስ የዜና ምንጭ ዘግቧል፡፡

በ8199 ነጻ የስልክ ጥሪ ማንኛውንም መረጃ እና ለጥያቄዎቻችሁ ምላሽ ስለሚገኝበት በመደወል እንድትጠቀሙ እናሳስባለን።




በታክስ እና በጉምሩክ ጉዳዮች ላይ መረጃ ለማግኘት 8199

### የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

### እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)